# በወንጀል ጉዳዮች የእርቅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2012

በእርቅ ማለቅ የሚችሉ ወንጀሎችን የወንጀል ምርመራ ከመጣራቱ በፊትም ሆነ ምርመራ ከተጣራ በኋላ ወይም ክስ ከተመሰረተ በኋላ ጉዳዩን በእርቅ መጨረሱ ወጪ ቆጣቢ፣ አስተማሪ፣ ማህበራዊ ግንኙነት ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል የሚያግዝ በመሆኑ፤

በእርቅ የሚያልቁ ጉዳዮችን በተመለከተ ወጥ አሰራር እንዲኖር፤ በእርቅ አፈፃፀም ሂደት ባለሙያዎቸ ሊከተሉት የሚገባቸዉን ስነ-ስርዓት ማስቀመጥ እና ግልፅነት ያለዉ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በቀድሞዉ ፍትህ ሚኒስቴር ሲሰራበት የነበረዉ "በወንጀል ጉዳዮች የእርቅ አሰራር መመሪያ ቁጥር 14/2007" ከፌደራል ጠቅላይ ዐ/ህግ አኳያ መቃኘት እና ማሻሻል በማስፈልጉ፤

የፌደራል ጠቅላይ ዐ/ህግ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 21(2) መሰረት ይህንን መመሪያ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በወንጀል ጉዳዮች የእርቅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. "የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 943/2008 የተቋቋመዉ የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ነዉ፡፡
2. . "ሓላፊ" ማለት በጠቅላይ ዐ/ህግ መስሪያ ቤት ዉስጥ ባሉ ዳይሬክቶሬቶች ዉስጥ ያሉ ዕ/ቤቶች እና ማስተባበሪያዎችን የሚራ ሃላፊ ወይም ምክትል ሃላፊ ነው፡፡
3. "መምሪያ" እና "ጣቢያ" ማለት እንደየቅደም ተከተላቸዉ በአዲስ አበባ ወይም በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ዉስጥ የሚገኝ የፖሊስ መምሪያ ወይም ጣቢያ ነዉ፡፡
4. "እርቅ" ማለት አንድ በወንጀል ሊያስከስስ የሚችል ጉዳይን የወንጀል ምርመራ ተጀመረ በኋላ፣ ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት ወይም ምርመራ ከመጀመሩ በፊት በተበዳዩ እና በተጠርጣሪዉ መካከል በሚደረግ ስምምነት መሰረት ክስ ሳይመሰረት እንዲቀር ወይም የተጀመረ ክስ እንዲቋረጥ የሚያስችል የህግ መሰረት ያለዉ አካሄድ ነዉ፡፡

5. "በባለሙያ ድጋፍ የሚደረግ ዕርቅ" ማለት የወንጀል ምርመራ ከመጀመሩ በፊት፣ ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት ወይም ምርመራ ካለቀ በኋላ ፖሊስ ወይም ዐ/ህግ ተሳትፎበት በጠቅላይ ዐ/ህግ መስሪያ ቤት ዉስጥ ወይም የፖሊስ መመሪያ ወይም ጣቢያ ዉስጥ የሚደረግ እርቅ ነዉ፡፡

6. "የዕርቅ ማመልከቻ" ማለት የጉዳዩ ባለቤቶች ወይም አቤቱታ አቅራቢዉ ከባለሙያ ድጋፍ ዉጭ በሆነ የእርቅ ሂደት ጉዳዩን መፍታቱን በመግለፅ የፖሊስ መዝገቡ እንዲዘጋለት የሚያስገባዉ ማመልከቻ ነዉ፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ እርቅ በህግ በተፈቀደባቸዉ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የእርቅ አፈፃፀም ሂደት

4. **በእርቅ ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች**

   1. በወንጀል ህጉ፣ በወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ወይም በሌላ ህግ ዉስጥ በግልፅ በእርቅ ለማለቅ እንደሚችል የተጠቀሰ ማንኛዉም ወንጀል እና ቀለል ያሉ ከህብረሰቡ ጥቅም ይልቅ የተበዳዩን ግለሰብ ጥቅም እና ደህንነት የሚመለከቱ በመሆናቸዉ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች በእርቅ ለማለቅ ይችላሉ፡፡
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ የተጠቀሰዉ ቢኖርም የዕርቅ ጥያቄዉ የቀረበዉ ወይም የእርቅ ሂደቱ እየተካሄደ ያለዉ በተበዳዩ ወይም በተከሳሹ ላይ በተደረገ መስገደድ፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ማታለል ወይም ሌሎች የባለጉዳዮችን ሙሉ ፍቃድ የሚያጓድሉ ነገሮች የተከሰቱ እንደሆነ እነዚሁ እልባት ሳያገኙ እርቅ መፈፀም አይቻልም፡፡
   3. በግል አቤቱታ ማመልከቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎችን በእርቅ ለመዝጋት የተከሳሽን የደጋጋሚነት ባህሪ እና ከሌላ ወንጀል ጋር ተደራርቦ የተፈፀመ መሆኑ ከልካይነት የለዉም፡፡
   4. በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በሆኑ ግዜ እና በእርቅ ለማለቅ እንደሚችሉ በህግ የተደነገጉ እንደሆነ የተከሳሹ ደጋጋሚነት እና ወንጀሉን ከሌላ ወንጀል ጋር ደርቦ የፈፀመዉ ከሆነ ዐ/ህግ አሁን በእርቅ ለመጨረስ ከታሰበዉ ጉዳይ ጋር ያለዉን ግንኙነት አይቶ እርቁን ለመከልከል ይችላል፡፡

5. **እርቅ ስለሚፈፀምበት ግዜ**

1. ማንኛዉም እርቅ ሊፈፀም የሚችለዉ የይርጋ ጊዜዉን ጠብቆ በቀረበ አቤቱታ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡
2. አንድ እርቅ የፖሊስ መዝገብ ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ ባሉት 14 ተከታታይ ቀናት ውስጥ መፈፀም አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2) የተቀመጠው ቢኖርም እርቁን ለመጨረስ ያላስቻለ በቂ ምክንያት ያጋጠመ እንደሆነ እና በመዝገቡ ላይ ሌላ ዉሳኔ መስጠቱ የሚኖረው ጠቀሜታ ያነሰ ከሆነ ከላይ የተቀመጠዉ የግዜ ገደብ ሳይከበር እርቅ ሊከናወን ይችላል፡፡
4. የዐ/ህግ ክስ በፍርድ ቤት መዝገብ ከተከፈተለት በኋላ ክስ በመሰማቱ ሂደት ውስጥ በቀጠሮ መካከል ባለጉዳዮች ታርቀዉ ወደ ዐ/ህግ መስሪያ ቤት ከመጡ የቀጠሮውን ቀን ሳይጠብቅ የክስ ሂደቱ የሚቋረጠዉ በሃላፊዎች ተፈርሞ ለፍርድ ቤት በሚቀርብ ማመልከቻ ይሆናል፡፡
5. የዐ/ህግ ክስ መታየት ከተጀመረ በኋላ ባለጉዳዮች መታረቃቸውን በችሎት ለፍርድ ቤቱ የሚያመለክቱ ከሆነ በችሎት ያለዉ ዐ/ህግ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(4) የተመለከተው የሃላፊ ደብዳቤ ሳያስፈልገዉ በጉዳዩ ላይ ስምምነቱን በመግለፅ መዝገቡ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 6. እርቅ ስለሚከናወንበት ቦታ

1. እርቅ የሚከናወነዉ የምርመራ መዝገቡን ለመወሰን እና ለመመርመር ስልጣን በተሰጣቸዉ ዐ/ህጎች ወይም መርማሪ ፖሊሶች ሆኖ በጠቅላይ ዐ/ህግ ጽ/ቤት ቢሮ፣ የፖሊስ መምሪያ ወይም ጣቢያ በሚገኝ አመቺ ቢሮ ዉስጥ መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠዉ ቢኖርም አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር ዐ/ህግ ወይም ፖሊስ ለቅርብ ኃላፊዉ በማሳወቅ ለእርቁ አመቺ በሆነ ሌላ ቦታ እርቁን ሊያከናዉን ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ የተቀመጠዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለጉዳዮች በመረጡት ቦታ በግላቸዉ እርቅ ፈጽመዉ በመምጣት የዕርቅ ማመልከቻ ሊያስገቡ ይችላሉ፡፡

## 7. የእርቅ አስፈፃሚዎች ሊከተሏቸዉ ስለሚገቡ አሰራሮች

ማንኛዉም የእርቅ አስፈፃሚ በእርቁ ወቅት የሚከተሉትን መርሆች መከተል አለበት፡-

1. በሁለቱም ወገን ያሉ ባለጉዳዮች ጉዳያቸዉን በእርቅ ለመጨረስ ፍቃደኛ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፤
2. ሁለቱም ወገኖች በዐ/ህግ መሰሪያ ቤት ወይም በፖሊስ መምሪያ ወይም ጣቢያ ተገኝተዉ ከሆነ መዝገቡ ላይ ማስረጃ መሰብሰብ ሳያስፈለዉ የእርቅ ስራዉ ሊሰራ

ይችላል፤ ነገር ግን ተከሳሽ ያልቀረበ ከሆነ ለእርቅ የሚጠራዉ መዝገቡ በማስረጃ የተደገፈ ከሆነ ብቻ ነዉ፤

3. ስለ እርቁ አካሔድ እና የህግ ዉጤት ለባለጉዳዮች በአግባቡ ማሳወቅ፤
4. የእርቅ ሂደቱን ግልፅ ማድረግ፣ በገለልተኛነት መምራት፣ በሂደቱ ያለመግባባት የተደረሰባቸዉን ነጥቦች ለመፍታት እንዲቻል እንደነገሩ ሁኔታ ጣልቃ በመግባት የማስታረቅ ሂደቱን ማገዝ፤
5. በባለሙያ ድጋፍ ባለጉዳዮች ስምምነት ላይ ከደረሱ ይህንን የሚገልፅ ሰነድ ጽፈዉ እና ተፈራርመዉ እንዲያስገቡ በማድረግ መዝገቡን በእርቅ መዝጋት፤
6. የእርቅ ስራዉ ከባለሙያ ድጋፍ ዉጭ በራሳቸዉ በባለጉዳዮች ተከናዉኖ የመጣ ከሆነ ዐ/ህግ እርቁ በአመልካቹ ሙሉ ፍቃድ መደረጉን በማረገገጥ መዝገቡን በእርቅ መዝጋት፤
7. የግል አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን መከታተል እንደማይፈልግ በፅሁፍ ከገለፀ ዐ/ህግ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 212 መሰረት መዝገብን ሊዘጋው ይችላል፡፡
8. ከላይ የተጠቀሱትን ሂደቶች ሁሉ የግል ተበዳይ በተወካዩ አማካኝነት ሊያከናዉን ይችላል፡፡

## 8. የእርቅ አፈፃፀም ስነ-ምግባር መርሆች

በህግ የተቀመጡ ሙያዊ የስነ ምግባር መርሆች እንደተጠበቁ ሆኖ የእርቅ አስፈፃሚዎች በእርቅ ሂደት ዉስጥ የሚከተሉትን የስነ ምግባር መርሆች ሊከተሉ ይገባል፡-

1. የእርቅ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ባለጉዳዮች ሙሉ ፍቃድ መስጠታቸዉን ማረጋገጥ እና በአካሄዱ ቅሬታ የሌላቸዉ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. በሂደቱ ለባለ ጉዳዮች እኩል የመሰማት መብት መስጠትና በትህትና ማስተናገድ፤
3. መፍትሔ ለመስጠት የተሻለ ጥቅም ከሌለዉ በቀር ባለጉዳዮችን ለየብቻ አለማነጋገር፤
4. በእርቅ ሂደቱ ለወንጀሉ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ ከስር መሰረቱ ሊፈታ በሚያስችል መልኩ መግባባት እንዲፈጠር መጣር፤
5. በእርቅ ሂደቱ የተገኙ ወይም የታወቁ ጉዳዮችን በሚስጥር ይዞ መጠበቅ እና ጉዳዩ በእርቅ ማለቅ ካልቻለ በመዝገቡ ላይ እንደ ማስረጃ አለመጠቀም፡፡

## 9. የእርቅ ስምምነት ስለሚፈርስበት ሁኔታ

1. በእርቅ የተዘጋ መዝገብ በባለጉዳዮች ላይ አስገዳጅነት ያለዉና የመጨረሻ ህጋዊ ውሳኔ ቢሆንም በሚከተሉት ምክንያቶች ፈራሽ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ እርቁ የተፈጸመዉ ከባለጉዳዮች በአንደኛዉ ወይም በሁለቱም ላይ በተደረገ ማናቸዉም ሙሉ ፍቃደኝነታቸዉን የሚሽረሽር/የሚያሳጣ ነገር መኖሩ በማስረጃ ሲረጋገጥ ወይም ዐ/ህጉ በነገሩ ካመነበት እና ስለዚሁ ነገር ቅሬታ ሲቀርብ፤

ለ/ በእርቅ ስምምነቱ ላይ የተገለፁ ወይም የተገቡ ቃሎች መፈፀም ሳይችሉ ሲቀሩ እና በዚህም የተነሳ ከተስማሚዎቹ አንዱ እርቅ እንዲፈርስለት የጠየቀ ሲሆን፤

ነዉ፡፡

2. ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች እርቅ ስምምነቱ የሚፈርስ ከሆነ ዐ/ህግ ይህንኑ መዝገብ ላይ እንዲሰፍር በማድረግ በመዝገቡ ላይ ተገቢ የሆነ ዉሳኔ ማስተላለፍ አለበት፡፡

## 10. የእርቅ ስምምነት ስለሚፈርስበት የግዜ ገደብ

በማንኛዉም ሁኔታ የእርቅ ስምምነቱን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች የተገኙ ሲሆን እርቁን ለማፍረስ የሚቻለዉ እርቁ በተፈፀመ በአንድ ወር ግዜ ዉስጥ ማመልከቻ ሲቀርብ ብቻ ነዉ፡፡

## 11. ሪፖርት ስለ ማቅረብ እና ተጠያቂነት

1. ማንኛዉም በእርቅ የተፈፀመ መዝገብ ለቅርብ ሀላፊ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ሪፖርት የተደረገለት ሀላፊ እርቁ ይህንን መመሪያ እና ሌሎች ህጎችን ባከበረ መልኩ የተደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ የእርቅ አፈጻጸሙ መመሪያዉን እና ሌሎች ህጎችን ያልተከተለ በሆነ ግዜ በነገሩ የተሳተፉ ባለሙያዎች በህግ መሰረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩልዩ ድንጋጌዎች

## 12. የተሻሩ ህጎች

1. የፍትህ ሚኒስቴር "በወንጀል ጉዳዮች የእርቅ አሰራር መመሪያ ቁጥር 14/2007" በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ምንኛዉም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

## 13. መመሪያዉ የሚፀናበት ግዜ

ይህ መመሪያ የስራ ሂደቶች ምክር ቤት ካፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡